# መጀመሪያዪቱ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች

## ምዕራፍ ፩

፩ከጳውሎስና ከስልዋኖስ፥ ከጢሞቴዎስም፥
በአባታችን በእግዚአብሔር፥ በጌታችን በኢየ
ሱስ ክርስቶስም ላመኑ በተሰሎንቄ ላሉ ማኅ
በረ ክርስቲያን፤ ከአባታችን ከእግዚአብሔርና
ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምና ጸጋ ለእ
ናንተ ይሁን።
፪ስለ እናንተ ዘወትር እግዚአብሔርን እናመሰ
ግነዋለን፤ ሁልጊዜም በጸሎታችን ሳናቋርጥ እና
ስባችኋለን። ፫በአባታችን በእግዚአብሔር ፊት
የሃይማኖታችሁን ሥራና የፍቅራችሁን ጽናት፥
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የሚሆን የተስፋ
ችሁንም ትዕግሥት እናስባለን። ፬የተወደዳችሁ
ወንድሞቻችን ሆይ፥ እግዚአብሔር እንደ መረ
ጣችሁ እናውቃለን። ፭የወንጌል ትምህርታችን
በኀይልና በመንፈስ ቅዱስ፥ በታመነ ምልጃም፩
እንጂ፥ በእናንተ ዘንድ በቃል ብቻ አይደለ
ምና፤ ስለ እናንተም በእናንተ ዘንድ የሆነውን
እናንተ ታውቃላችሁ። ፮እነሆ፥ እናንተም እኛ
ንና ጌታን መሰላችሁ፤ በብዙ መከራ ከመን
ፈስ ቅዱስ ደስታ ጋር ቃሉን ተቀብላችኋልና።
፯በመቄዶንያና በአካይያ ላሉ ምእመናን ሁሉ
ምሳሌ ሆናችኋል። ፰የጌታችንን ቃል ከእናንተ
ሰምተው ተምረዋልና፤ ነገር ግን በመቄዶንያና
በአካይያ ብቻ አይደለም፤ ደግሞም በእግዚአብ
ሔር ማመናችሁ በየገሩ ተሰምታለች፤ እኛም
ስለ እናንተ ምንም ልንናገር አንሻም። ፱እኛ
ወደ እናንተ እንደ መጣን፥ እናንተም ለሕያ
ውና ለእውነተኛ አምላክ ታገለግሉ ዘንድ፥ ከጣ
ዖት አምልኮ ወደ እግዚአብሔር እንደ ተመለ
ሳችሁ እነርሱ ራሳቸው ያውቃሉ። ፲ከሙታን
ተለይቶ የተነሣ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን ከሰ
ማያት ተስፋ እያደረጋችሁ፥ እርሱም ከሚመ
ጣው መከራ ያድነናል።

## ምዕራፍ ፪

### ጳውሎስ በተሰሎንቄ ወንጌልን እንደ አስተማረ

፩ወንድሞቻችን ሆይ፥ ያደረግንላችሁን፩ እና
ንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁ፤ ወደ እናንተ መግ
ባታችንም በከንቱ አይደለም። ፪እንደምታው
ቁትም በፊልጵስዩስ መከራ ተቀበልን፤ ተሰደ
ብን፤ ያንጊዜም በአምላካችን ደፍረን፥ የክርስ
ቶስን ወንጌል በብዙ ገድል አስተማርናችሁ።
፫ትምህርታችን፪ የስሕተትና የርኵሰት፥ የሽንገ
ላም አይደለምና፤ ፬ነገር ግን እግዚአብሔር ስለ
ፈተነንና ወንጌሉን ለማስተማር የታመነ ስለ
አደረገን እንዲህ እናስተምራለን፤ ሰውን ደስ
ለማሰኘት እንደሚሠራም አይደለም፤ ልቡናች
ንን ለመረመረው ለእግዚአብሔር ነው እንጂ።
፭ከሆነም ጀምሮ እንደምታውቁት በቃል አልሸ
ነገልናችሁም፤ በምክንያትም አልቀማናችሁም፤
በዚህም እግዚአብሔር ምስክራችን ነው። ፮የክ
ርስቶስ ሐዋርያት እንደ መሆናችን ልናከብድ
ባችሁ ሲቻለን ከእናንተም ቢሆን፥ ከሌላም
ቢሆን ከሰው ክብርን አንፈልግም። ፯ነገር ግን
በመካከላችሁ እንደ ሕፃናትና ልጆችዋን እንደ
ምታሳድግ እንደ ሞግዚት ሆንን፤ ከሰው ክብ
ርን አንፈልግም። ፰እኛም እንዲሁ እንወዳችኋ
ለን፤ የእግዚአብሔርን ወንጌል ብቻ ሳይሆን፥

---

፩ ግሪኩ "በብዙ መረዳት" ይላል።

፩ "ያደረግንላችሁን" የሚለው በግሪኩ የለም።

፪ ግሪኩ "ምልጃችን" ይላል።

፩፥፩ ሐ.ሥ. ፲፯፥፩።   ፩፥፮ ሐ.ሥ. ፲፯፥፭-፱።   ፪፥፪ ሐ.ሥ. ፲፮፥፲፱-፳፬፤ ፲፯፥፩-፱።

ሰውነታችንንም ጭምር ልንሰጣችሁ እናስብላች
ኋለን፤ ወዳጆች ሆናችሁናልና።
፱ወንድሞቻችን ሆይ፥ ድካማችንንና ጥረታች
ንን አስቡ፤ ከእናንተ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብ
ድበት በቀንና በሌሊት እየሠራን የእግዚአብሔ
ርን ወንጌል ሰበክንላችሁ። ፲በምታምኑት በእ
ናንተ ሁሉ ዘንድ በእውነትና በቅንነት፥ በንጽ
ሕናም እንደ ሄድን እናንተ ራሳችሁ ምስክሮ
ቻችን ናችሁ፤ እግዚአብሔርም ምስክር ነው።
፲፩ከእናንተ እያንዳንዳችሁ እንደምታውቁት፥
አባት ለልጁ እንደሚያደርግ እንማልዳችኋለን፤
እናረጋጋችኋለንም። ፲፪ወደ ጌትነቱ መንግሥት
ወደ ጠራችሁ እግዚአብሔር በሚገባችሁ ትሄዱ
ዘንድ እናዳኝባችኋለን።
፲፫ስለዚህም እኛ ዘወትር እግዚአብሔርን እና
መሰግነዋለን፤ ከእኛ የሰማችሁትን እግዚአብ
ሔር ያዘዘውን ቃል ተቀብላችኋልና፤ የሰው
ንም ቃል አይደለም፤ ነገር ግን ያመናችሁትን
እናንተን በሥራ የሚረዳችሁ በእውነት የእግ
ዚአብሔር ቃል ነው። ፲፬እናንተም ወንድሞቻ
ችን፥ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው፥ በይሁዳ
ያሉትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን መሰ
ላችሁ፤ እነርሱ ከአይሁድ መከራን እንደ ተቀ
በሉ፥ እናንተም ከወገኖቻችሁ መከራን ተቀብ
ላችኋልና። ፲፭እነርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስ
ቶስን የገደሉት ናቸው፤ በመካከላቸው የነበሩ
ነቢያትንም፥ እኛንም አሳደዱ፤ እግዚአብሔ
ርንም ደስ አያሰኙትም፤ ከሰው ሁሉ ጋርም
ይጣላሉ። ፲፮ኀጢአታቸው አዘውትሮ ይፈጸም
ባቸው ዘንድ፥ ለአሕዛብ የሚድኑበትን እንዳንነ
ግራቸው ይከለክሉናል፤ እነሆ፥ ለዘለዓለም የሚ
ሆን መቅሠፍታቸውም ደረሰባቸው።

## ቅዱስ ጳውሎስ የተሰሎንቄን ምእመናን ለማየት እንደ ናፈቀ

፲፯ወንድሞቻችን ሆይ፥ እኛስ በዚህ ወራት
ከእናንተ የተነጣ እንደ ሙት ልጅ ሆን፤ ከፊት
ነው እንጂ ከልብ አይደለም፤ ፊታችሁንም
ልናይ እጅግ ናፍቀናል። ፲፰ ፫እኔ ጳውሎስ አንድ
ጊዜና ሁለት ጊዜ ወደ እናንተ ልመጣ ብዙ
ወደድሁ፤ ነገር ግን ሰይጣን አሰናከለኝ። ፲፱አለ
ኝታችንና ደስታችን፥ የትምክሕታችን አክሊ
ልስ ማን ነው? በሚመጣበት ጊዜ በጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት እናንተ አይደላችሁምን?
፳ክብራችንና ደስታችን እናንተ ናችሁና።

## ምዕራፍ ፫

## ጢሞቴዎስ ወደ ተሰሎንቄ እንደ ተላከ

፩መታገሥ ስለ ተሳነንም ብቻችንን በአቴና
ልንኖር ወደድን። ፪በክርስቶስ ወንጌል የሚረ
ዳንን የእግዚአብሔርን አገልጋይ ወንድማችን
ጢሞቴዎስን ስለ ሃይማኖታችሁ እንዲያጽናናች
ሁና እንዲመክራችሁ ላክነው፤ ፫ከእናንተ አንዱ
ስንኳ በዚች በመከራችሁ እንዳይናወጥ፥ ተስ
ፋም እንዳይቈርጥ፥ እናንተ ራሳችሁ ይህ ብቻ
እንደሚቈየን ታውቃላችሁና። ፬በእናንተ ዘንድ
በነበርንበት ጊዜ መከራ እንደምንቀበልና እንደ
ሚያሠቃዩን፥ አስቀድመን ይህን ብቻ ነገርና
ችሁ፤ እንደ ነገርናችሁም ያው ሆነ፤ ይህንም
ታውቃላችሁ። ፭ስለዚህም እኔ መታገሥ ተስ
ኖኝ፥ ምናልባት ፈታኝ ፈትኖአችኋል፤ ድካማ
ችንም ለከንቱ ሆኖአል ብዬ ሃይማኖታችሁን
አውቅ ዘንድ ጢሞቴዎስን ላክሁት።
፮አሁን ግን ጢሞቴዎስ ከእናንተ ወደ እኛ
ተመልሶ ሃይማኖታችሁንና ፍቅራችሁን፥ በመ
ልካምም ዘወትር እንደምታስቡን፥ እኛ እናን
ተን ልናያችሁ እንደምንናፍቅ ሁሉ፥ እናን
ተም ልታዩን እንደምትናፍቁ በነገረን ጊዜ፥
፯ስለዚህ ወንድሞቻችን፥ ስለ ሃይማኖታችሁ
በተቀበልነው በመከራችንና በችግራችን ሁሉ
ተጽናናን። ፰እናንተ በጌታችን ጸንታችሁ ብት
ቆሙ፥ አሁን እኛ በሕይወት እንኖራለንና።
፱በእናንተ ምክንያት በአምላካችን ፊት ደስ ስለ
አለን ደስታ ሁሉ ስለ እናንተ ለእግዚአብሔር
ምን ምስጋና ልናቀርብለት እንችላለን? ፲ፊታ
ችሁን ለማየት ሌሊትና ቀን አብዝተን እንጸል
ያለን፤ ሃይማኖታችሁም ፍጹም ይሆን ዘንድ
እንለምናለን።
፲፩እግዚአብሔር አባታችን፥ ጌታችን ኢየሱስ
ክርስቶስም ወደ እናንተ መንገዳችንን ያቅና
ልን። ፲፪እኛ እናንተን እንደምንወዳችሁ፥ ጌታ
ችን እርስ በርሳችሁ ያላችሁን፥ ከሁሉም ከእያ
ንዳንዱ ጋር የሚሆን ፍቅራችሁን ያብዛላችሁ፤
ይጨምርላችሁም። ፲፫ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
ከቅዱሳን ሁሉ ጋር በሚመጣበት ጊዜ፥ በአባ

---

፫ ግሪኩ "ስለዚህም ወደ እናንተ ልንመጣ ወድደን ነበር" የሚል ይጨምራል።

፪፥፲፬ ሐ.ሥ. ፲፯፥፭። ፪፥፲፭ ሐ.ሥ. ፱፥፳፫፤ ፳፱፤ ፲፫፥፵፭፤ ፲፬፥፪፤ ፭፤ ፲፱፤ ፲፯፥፭፤ ፲፫፤ ፲፰፥፲፪።

፫፥፩ ሐ.ሥ. ፲፯፥፲፭። ፫፥፮ ሐ.ሥ. ፲፰፥፭። ፫፥፯ ፪ቆሮ. ፩፥፬። ፫፥፲ ፪ቆሮ. ፲፫፥፱።

ታችን በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም ልባችሁ
በንጽሕናና በቅድስና ይጽና።

## ምዕራፍ ፬

### በጎ ምክር

፩እሁንም ወንድሞቻችን ሆይ፥ በእኛ ዘንድ
እንደ ታዘዛችሁ በሚገባ ትሄዱ ዘንድ፥ እግዚ
አብሔርንም ደስ ታሰኙ ዘንድ፥ ደግሞ እንደ
ሄዳችሁ ከፊት ይልቅ በዚሁ ታበዙና ትጨምሩ
ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንነግራች
ኋለን፤ እንማልዳችኋለንም። ፪በጌታችን በኢየ
ሱስ ክርስቶስም ያዘዝናችሁን ትእዛዝ ታውቃ
ላችሁ። ፫የእግዚአብሔር ፈቃድ ይህ ነውና፤
እርሱም ከዝሙት ትርቁ ዘንድ መቀደሳችሁ
ነው። ፬ሁሉም እያንዳንዱ ገንዘቡን ይወቅ፤ በን
ጽሕናና በክብርም ይጠብቀው። ፭እግዚአብሔ
ርን እንደማያውቁት እንደ አረማውያንም በፍት
ወት ድል አትነሡ። ፮ይህንም ለማድረግ አትደ
ፋፈሩ፤ በሁሉም ወንድሞቻችሁን አትበድሉ፤
አስቀድሜ እንደ ነገርኋችሁና እንደ አዳኘሁ
ባችሁ፥ በዚህ ሁሉ እግዚአብሔር የሚበቀል
ነውና። ፯እግዚአብሔር ለቅድስና እንጂ ለርኵ
ሰት አልጠራንምና። ፰አሁንም የሚክድ፥ መን
ፈስ ቅዱስን የሰጣችሁን እግዚአብሔርን እንጂ
ሰውን የካደ አይደለም።

፱ባልንጀሮቻችሁን ስለ መውደድ ግን ልንጽፍ
ላችሁ አያስፈልጋችሁም፤ እርስ በርሳችሁ እን
ድትዋደዱ ራሳችሁ በእግዚአብሔር የተማራችሁ
ናችሁና። ፲በመቄዶንያ ሁሉ ካሉት ወንድሞቻ
ችን ሁሉ ጋር እንዲሁ ታደርጋላችሁ፤ ነገር ግን
ወንድሞቻችን ሆይ፥ ትበዙና ትጨምሩ ዘንድ
እንማልዳችኋለን። ፲፩የዋህንም ትሆኑ ዘንድ፥፩
ሥራችሁንም ታከናውኑ ዘንድ እንደ አዘዝናች
ሁም በእጃችሁ ትሠሩ ዘንድ፥ ፲፪በውጭ ባሉት
ሰዎችም ዘንድ ከማንም አንዳች ሳትሹ በሚገባ
ትመላለሱ ዘንድ እንለምናችኋለን።

### ስለ ጌታ ዳግም ምጽአት

፲፫ወንድሞቻችን ሆይ፥ ስለ ሞቱ ሰዎች፥
ተስፋ እንደሌላቸው ሰዎች እንዳታዝኑ ልታ
ውቁ እንወዳለን። ፲፬ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ
እንደ ተነሣ ካመንን፥፪ እንዲሁ እግዚአብሔር
ሙታንን በኢየሱስ ያስነሣቸዋል፤ ከእርሱም
ጋር ያመጣቸዋል። ፲፭ይህንም በእግዚአብሔር
ቃል እንነግራችኋለን፤ ጌታችን በሚመጣ ጊዜ
ሕያዋን ሆነን የምንቀር እኛ የሞቱትን አንቀድ
ማቸውም። ፲፮ጌታችን ራሱ በትእዛዝ፥ በመላእ
ክትም አለቃ ድምፅ፥ በእግዚአብሔርም መለ
ከት ከሰማይ ይወርዳልና፤ በክርስቶስም የሞቱ
ሙታን አስቀድመው ይነሣሉ። ፲፯ከዚያም በኋላ
እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታችንን በአ
የር እንቀበለው ዘንድ ከእርሱ ጋር በደመና እን
ነጠቃለን። ከዚያም ወዲያ ለዘለዓለሙ ከጌታ
ችን ጋር እንኖራለን። ፲፰ስለዚህ እርስ በርሳችሁ
በዚህ ቃል ተጽናኑ።

## ምዕራፍ ፭

### የጌታ ዳግም ምጽአት ድንገት እንደሚደርስ

፩ወንድሞቻችን ሆይ፥ ስለ ዘመኑና ስለ
ወራቱ፥ ስለ ቀኑም፥ ልንጽፍላችሁ አያስፈልጋ
ችሁም፤ ፪የጌታችን ቀን ሌባ በሌሊት እንደሚ
መጣ እንዲሁ ትመጣ ዘንድ እናንተ ራሳችሁ
በርግጥ ታውቃላችሁና። ፫ሰላምና ደኅንነት ነው
ሲሉ ያንጊዜ ምጥ የፀነሰችን ሴት እንደሚይ
ዛት፥ ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል፤ ማም
ለጥም አይቻላቸውም፤ ፬እናንተ ግን ወድሞቻ
ችን ሆይ፥ ቀኑ እንደ ሌባ ይደርስባችሁ ዘንድ
በጨለማ ውስጥ አይደላችሁም። ፭ሁላችሁም
የብርሃን ልጆች፥ የቀንም ልጆች ናችሁና፤ እኛ
ከሌሊት፥ ወይም ከጨለማ አይደለንም። ፮እን
ግዲህ እንንቃ፤ እንትጋ፤ እንወቅም እንጂ እንደ
እነዚያ አናንቀላፋ። ፯የሚያንቀላፉ በሌሊት ያን
ቀላፋሉና፤ የሚሰክሩም በሌሊት ይሰክራሉና።
፰እኛ ግን የቀን ልጆች ስለሆን እንንቃ፤ የሃይ
ማኖትንና የፍቅርን ጥሩር እንልበስ፤ ተስፋ ያለ
በት የመዳንን ራስ ቍርም እንቀዳጅ። ፱እግዚ
አብሔር በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለሕይወ
ትና ለደኅንነት እንጂ፥ ለጥፋት አላደረገንምና።
፲የምንነቃ፥ ወይም የምናንቀላፋ ብንሆን፥ ሁላ
ችን ከእርሱ ጋር በሕይወት እንኖር ዘንድ፥ ስለ

---

፩ ግሪኩ "በፀጥታ ትኖሩ ዘንድ" ይላል።
፪ ግሪኩ "እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋል" ይላል።
፬፥፩ ፊልጵ. ፩፥፳፯። ፬፥፭ ሮሜ. ፩፥፳፬፤ መዝ. ፸፱፥፮፤ ኤር. ፲፥፳፭። ፬፥፱ ኤር. ፴፩፥፴፬።
፬፥፲፫-፲፯ ፩ቆሮ. ፲፭፥፶፩-፶፪። ፭፥፪ ማቴ. ፳፬፥፵፫፤ ሉቃ. ፲፪፥፴፱፤ ፪ጴጥ. ፫፥፲።
፭፥፰ ኢሳ. ፶፱፥፲፯፤ ኤፌ. ፮፥፲፫-፲፯።

እኛ ቤዛ ሆኖ ሞተ። ፲፩እሁንም ስለዚህ እናንተ
እንደምታደርጉ ወንድሞቻችሁን እጽናኑ። እን
ዱም እንዱም ወንድሙን ያንጸው።

## የመጨረሻው ስላምታና ማጽናናት

፲፪ወድሞቻችን ሆይ፥ በመካከላችሁ የሚደክ
ሙትን፥ በጌታችን የሚቆሙላችሁንና የሚአ
ስተምሩአችሁንም ዕወቋቸው ብለን እንማልዳ
ችኋለን። ፲፫እጅግ አክብሩአቸው፤ ስለ ሥራቸ
ውም ውደዱአቸው፤ እርስ በርሳችሁም በሰላም
ሁኑ። ፲፬ወንድሞቻችን፥ እንማልዳችኋለን፤ ያለ
ሥርዐት የሚሄዱትንም ገሥጹአቸው፤ ያዘኑት
ንም አረጋጉአቸው፤ የደከሙትን እጽኑአቸው፤
ሁሉንም ታገሡ። ፲፭በክፉ ፋንታ ክፉ እንዳታ
ደርጉ ተጠንቀቁ፤ ነገር ግን ዘወትር እርስ በር
ሳችሁ ለሌላው መልካም ነገርን ትሠሩ ዘንድ
ተሽቀዳደሙ። ፲፮ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ። ፲፯ያለ
ማቋረጥም ጸልዩ። ፲፰ስለ ሥራው ሁሉ እግዚ
እብሔርን አመስግኑት፤ ስለ እናንተ የእግዚእ
ብሔር ፈቃዱ በኢየሱስ ክርስቶስ ይህ ነውና።
፲፱መንፈስን አታጥፉ። ፳ትንቢትንም አትናቁ።
፳፩ሁሉን መርምሩ፤ መልካም የሆነውንም ያዙ።
፳፪ከክፉ ሥራ ሁሉ ራቁ።
፳፫የሰላም አምላክ እግዚአብሔር ፈጽሞ ይቀ
ድሳችሁ፤ ነፍሳችሁን፥ መንፈሳችሁንና ሥጋች
ሁንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት
ጊዜ በንጽሕና ይጠብቅ። ፳፬የጠራችሁ እርሱም
ይህን ያደርግላችሁ ዘንድ የታመነ ነው።
፳፭ወንድሞቻችን ሆይ፥ ጸልዩልን። ፳፮በተቀ
ደሰ ሰላምታም ወንድሞቻችንን ሁሉ ሰላም
በሉ፤ እርስ በእርሳችሁም ሰላም ተባባሉ።[፩]
፳፯ይህችን መልእክት ለቅዱሳን ወንድሞቻችን
ሁሉ ታነቡእት ዘንድ በጌታችን አምላችኋለሁ።
፳፰የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ
ጋር ይሁን፤ አሜን።

ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች የተላከ መጀመሪያይዉ
መልእክት ተፈጸመ፤

በእቴና ተጻፈ፤ በጢሞቴዎስና በስልዋኖስ
እጅም ተላከ።

ስእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። አሜን።

፩ “እርስ በእርሳችሁም ሰላም ተባባሉ” የሚለው በግሪኩ የለም።

# ሁለተኛው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች

## ምዕራፍ ፩

፩ከጳውሎስ፥ ከስልዋኖስና ከጢሞቴዎስ በአ
ባታችን በእግዚአብሔር፥ በጌታችን በኢየሱስ
ክርስቶስ ላመኑ በተሰሎንቄ ላሉ ማኅበረ ክር
ስቲያን፤ ፪የአባታችን የእግዚአብሔር፥ የጌታ
ችን የኢየሱስ ክርስቶስም ሰላምና ጸጋ ለእና
ንተ ይሁን።

፫ወንድሞቻችን ሆይ፥ እንደሚገባ ስለ እናንተ
ዘወትር እግዚአብሔርን ልናመሰግነው ይገባል፤
ሃይማኖታችሁ እድጋለችና፥ ከባልንጀራችሁም
ሁሉ ጋር ፍቅራችሁ በዝታለችና። ፬ስለዚህ በም
ትታገሡበት በስደታችሁና በመከራችሁ ስለ
ሃይማኖታችሁና ስለ ትዕግሥታችሁ በእግዚአብ
ሔር አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በእናንተ እን
መካለን። ፭እግዚአብሔር መከራ የምትቀበሉለ
ትን መንግሥቱን ያድላችሁ ዘንድ ይህ የእግዚ
አብሔር የእውነተኛ ፍርዱ ምልክት ነው።

### ስለ ጌታችን መምጣት

፮መከራ የሚያጸኑባችሁ እነዚያ በእግዚአብ
ሔር ዘንድ ፍዳቸውን ይቀበሉ ዘንድ ይገባል።
፯ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኀይሉን ከሚገልጥባ
ቸው መላክእቱ ጋር በሚመጣበት ጊዜ፥ መከራ
ለምትቀበሉ ለእናንተ ከእኛ ጋር ዕረፍት ይገባ
ችኋል። ፰እግዚአብሔርን የማያውቁትን፥ የጌ
ታችን የኢየሱስ ክርስቶስንም ወንጌል የማይሰ
ሙትን ይበቀላቸዋል። ፱ከጌታችን ፊት፥ ከኀይ
ሉም ክብር ርቀው የዘለዓለም ጥፋት ፍዳቸውን
ያገኛሉ። ፲በቅዱሳኑ ይከበር ዘንድ፥ በሚያምኑ
ትም ይመሰገን ዘንድ በሚመጣ ጊዜ፥ በዚያች
ቀን ለእናንተ የመሰከርነው ምስክርነታችን ይታ
መንልናልና። ፲፩ስለዚህ እግዚአብሔር ለመጥ
ራቱ የተገባችሁ ያደርጋችሁ ዘንድ፥ ይቅርታው
ንና በጎነቱን፥ የእምነትንም ሥራ በኀይል ይፈ
ጽምላችሁ ዘንድ ዘወትር እንጸልያለን። ፲፪እንደ
አምላካችንና እንደ ጌታችን እንደ ኢየሱስ ክርስ
ቶስ ጸጋ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም በእ
ናንተ ላይ ይከብር ዘንድ፥ እናንተም በእርሱ
ትከብሩ ዘንድ እንጸልያለን።

## ምዕራፍ ፪

### ስለ ሐሳዊ መሲሕ

፩ወንድሞቻችን ሆይ፥ ስለ ጌታችን ስለ ኢየ
ሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱ ስለ መሰ
ብሰባችን እንነግራችኋለን። ፪"በመንፈስ ወይም
በቃል፥ ወይም ከእኛ እንደሚመጣ፥ በመልእ
ክት የጌታ ቀን ደርሶአል" ብላችሁ ከአእምሮ
ፈጥናችሁ እንዳትናወጡ፥ እንዳትደነግጡም
ዕወቁ። ፫በምንም የሚያስታችሁ አይኑር፤ ክህ
ደት ሳይመጣና የዐመፅ ሰው እርሱም የጥፋት
ልጅ ሳይገለጥ ያቺ ቀን አትመጣምና። ፬ራሱን
ከፍ ከፍ የሚያደርግ፥ ለሁሉም እኔ እግዚአብ
ሔር አምላክ ነኝ የሚል፥ በእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ የሚቀመጥ፥ ራሱንም እንደ እግዚአ
ብሔር የሚያደርግ ተቃዋሚ ነው። ፭በእናንተ
ዘንድ በነበርሁ ጊዜ፥ አስቀድሜ ይህን እንደ
ነገርኋችሁ አታስቡምን? ፮ጊዜው እስኪደርስ
ድረስ ከመታየት የሚከለክለውን አሁን ታውቃ
ላችሁ። ፯የኀጢአት ምሥጢር በእርሱ ፈጽሞ
ይሠራልና፤ ዛሬ ግን ከመካከል እስኪወገድ
ድረስ ተይዞአል። ፰ያንጊዜም የጌታችን የኢየ
ሱስ ክርስቶስ መንፈሱ ያጠፋው ዘንድ ያለው፥
ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ኀጢአተኛው
የዐመፅ ልጅ ይገለጣል። ፱የዚያ ሰው አመጣጡ

---

፩፥፩ ሐ.ሥ. ፲፯፥፩። ፩፥፰ ኢሳ. ፷፮፥፲፭። ፩፥፱ ኢሳ. ፪፥፲። ፪፥፩ ፩ተሰ. ፬፥፲፭-፲፯።
፪፥፬ ዳን. ፲፩፥፴፮፤ ሕዝ. ፳፰፥፪። ፪፥፰ ኢሳ. ፲፩፥፬። ፪፥፱ ማቴ. ፳፬፥፳፬።

በሰይጣን ሥራ፥ በኀይል ሁሉና በምልክት፥
የሐሰት ድንቅ ሥራዎችንም በመሥራት ነው።
[፲]ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ
ለሚጠፉትም በዐመፅ ማታለል ነው። [፲፩]ስለዚ
ህም እግዚአብሔር በሐሰት ያምኑ ዘንድ የሚ
ያስት ኀይልን ይልክባቸዋል። [፲፪]በእውነት የማ
ያምኑና በዐመፅ የሚተባበሩ ሁሉ ይፈረድባ
ቸው ዘንድ።

### ስለ ምእመናን እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባ

[፲፫]በእግዚአብሔር የተመሰገናችሁ ወንድሞቻ
ችን ሆይ፥ ስለ እናንተ ዘወትር እግዚአብሔርን
ልናመሰግነው ይገባል፤ እግዚአብሔር በመንፈስ
መቀደስ፥ እውነትንም በማመን ለመዳን በዙር
አድርጎ መርጦአችኋልና። [፲፬]ለዚህም የጌታችን
የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ለማግኘት በወንጌል
ትምህርት ጠራችሁ። [፲፭]እሁንም ወንድሞቻችን
ሆይ፥ ጸንታችሁ ቁሙ፤ በቃላችንም ቢሆን፥
ወይም በመልእክታችን ያስተማርናችሁንና የሠ
ራንላችሁን ሥርዐት ያዙ።
[፲፮]ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የወደደን፥
የዘለዓለምን መጽናናትና መልካም ተስፋንም
የሰጠን እግዚአብሔር አባታችን፥ [፲፯]እርሱ በጸ
ጋው ልባችሁን ያጽና፤ በበጎ ምግባርና በቃ
ልም ሁሉ ያጽናችሁ።

## ምዕራፍ ፫

### ስለ ወንጌል መስፋፋት ጸሎት

[፩]እሁንም ወንድሞቻችን ሆይ፥ በእናንተ
ዘንድ እንደ ሆነው የእግዚአብሔር ቃል እን
ዲፋጠንና እንዲከብር ጸልዩልን። [፪]ከክፉዎችና
ከከሐዲዎች ሰዎችም እንድን ዘንድ ጸልዩልን፤
ሁሉ አማኝ አይደለምና። [፫]ነገር ግን የሚያጸ
ናችሁና ከክፉ ሁሉ የሚጠብቃችሁ እግዚአብ
ሔር የታመነ ነው። [፬]ያዘዝናችሁን እንድታደ
ርጉ በእግዚአብሔር እንተማመናችኋለን፤ ታደ
ርጉታላችሁም። [፭]ጌታችንም፥ ወደ እግዚአብ
ሔር ፍቅር ወደ ክርስቶስም ትዕግሥት ልባች
ሁን ያቅና።

### ሥራ ፈት መሆን እንደማይገባ

[፮]ወንድሞቻችን ሆይ፥ በሠራንላቸው ሥርዐት
ሳይሆን በተንኰል ከሚሄዱት ወንድሞች ሁሉ፥
ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም
እናዝዛችኋለን። [፯]እኛን ልትመስሉ እንደሚገባ
ችሁ፥ እኛም በእናንተ መካከል ያለ ሥራ እን
ዳልኖርን[፩] ራሳችሁ ታውቃላችሁ። [፰]በእናንተ
ላይ እንዳንከብድባችሁ፥ ቀንና ሌሊት በድካ
ምና በጥረት እየሠራን እንጂ የሌላውን እህል
በከንቱ አልበላንም። [፱]ይህም እኛን ልትመስሉን
ምሳሌ እንድንሆናችሁ ነው እንጂ ያለ ሥልጣን
ስለ ሆንን አይደለም። [፲]በእናንተ ዘንድ በነበርን
ጊዜም "ሊሠራ የማይወድ አይብላ" ብለን አዝ
ዘናችሁ ነበርና። [፲፩]በውስጣችሁ በስንፍና የሚ
ኖሩ እንዳሉ ሰምተናል፤ የሚሠሩትም ሥራ የላ
ቸውም፤ ደግሞም ዘዋሪዎች ናቸው። [፲፪]እንደ
እነዚህ ያሉትንም በጸጥታ ሥራቸውን እየሠሩ
የገዛ ምግባቸውን ይመገቡ ዘንድ፥ በጌታችን
በኢየሱስ ክርስቶስ እናዝዛቸዋለን፤ እንመክራ
ቸዋለንም። [፲፫]ወንሞቻችን ሆይ፥ እናንተ ግን
ሁልጊዜ ሥራ መሥራትን ቸል አትበሉ።
[፲፬]ለቃላችንና ለመልእክታችን የማይታዘዝ
ቢኖር ይለይ፤ እንዲያፍርም አትጨመሩት።
[፲፭]ነገር ግን ወንድማችሁ እንደ መሆኑ ምከሩት
እንጂ፥ እንደ ጠላት አታድርጉት።
[፲፮]የሰላም አምላክ እርሱ ሁልጊዜ በሥራው
ሁሉ ሰላምን ይስጣችሁ፤ ጌታችንም ከሁላ
ችሁ ጋር ይኑር። [፲፯]እኔ ጳውሎስ ይህን ሰላ
ምታ በእጄ ጻፍሁ፤ በመልእክቶቼ ሁሉ ምል
ክቴ ይህ ነው፤ እንዲህ እጽፋለሁ። [፲፰]የጌታ
ችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር
ይሁን፤ አሜን።

ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች የተላከ ሁለተኛዉ መልእክት ተፈጸመ፤ በሎዶቅያ ተጻፈ በቲኪቆስ እጅ ተላከ።

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። አሜን።

---

፩ ግእዙ "በእናንተ ላይ እንዳልሳሳን" ይላል።

፫፥፩ ቆላ. ፬፥፫። ፫፥፮ ማቴ. ፲፰፥፲፯። ፫፥፲ ዘፍ. ፫፥፲፱። ፫፥፲፯ ፩ቆሮ. ፲፮፥፳፩።

# መጀመሪያው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ጢሞቴዎስ

## ምዕራፍ ፩

፩በመድኀኒታችን በእግዚአብሔር፥ በተስፋችን በኢየሱስ ክርስቶስም ትእዛዝ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ከሚሆን ከጳውሎስ፥ ፪በሃይማኖት ለምወድህ[፩] ልጄ ለጢሞቴዎስ፥ የአባታችን የእግዚአብሔርና የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም፥ ጸጋና ምሕረት ለአንተ ይሁን።

፫ወደ መቄዶንያ በሄድሁ ጊዜ በኤፌሶን እንድትቀመጥ ለምኜህ ነበር። ትገሥጻቸው ዘንድ ሌላ ትምህርት እንዳያመጡ፥ ፬ፈጥረው የሚናገሩትንም ተረትና ጨዋታ[፪] እንዳያመጡ፤ እነርሱም ሊያስቱ ክርክርን ያመጣሉ፤ በሃይማኖት ያለውንም የእግዚአብሔርን ሕግ ይተዋሉ። ፭የትእዛዝ ፍጻሜ ግን በንጹሕ ልብና በመልካም ጠባይ፥ ጥርጥር በሌለበትም እምነት መፋቀር ነው። ፮ከዚህ ወጥተው ወደ ከንቱ ነገር የተመለሱ አሉና። ፯የሕግ መምህራን ሊሆኑ ሲወዱ ራሳቸው የሚናገሩትንና የሚያስረዱትን እያውቁም።

፰ኦሪት እንደሚገባ ለሚሠራበት መልካም እንደ ሆነ እናውቃለን። ፱ሕግ የሚሠራ ለጻድቃን እንዳይደለ ይህን እናውቃለን፤ ለኀጢአተኞችና ለከዳተኞች፥ ኀጢአትን ለሚያዘወትሩና ከእውነት ለወጡ፥ ለርኩሳን፥ አባታቸውንና እናታቸውን ለሚገድሉ ነፍስ ገዳዮችም፥ ፲ለሴሰኞችና ለእመንዝራዎች፥[፫] ሰውን ለሚሰርቁ፥ ሐሰት ለሚናገሩና በሐሰት ለሚምሉም ነው እንጂ። ፲፩የቡሩክ እግዚአብሔርንም ክብር የሚገልጥ ለእኔ አደራ የተሰጠኝ የወንጌልን የሕይወት ትምህርት ለሚቃወሙም ነው እንጂ።

### ቅዱስ ጳውሎስ ስለ መጠራቱ ያቀረበው ምስጋና

፲፪ያጸናኝን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አመሰግነዋለሁ፤ ለመልእክቱ ሾሞ ታማኝ አድርጎኛልና። ፲፫እኔ ቀድሞ ተሳዳቢና አሳዳጅ፥ ተቃዋሚም ስሆን፥ ሳላውቅ ባለ ማመን ስለ አደረግሁት ይቅር አለኝ። ፲፬የእግዚአብሔር ጸጋው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከማመንና ከመውደድ ጋር በእኔ ላይ በዛ። ፲፭ነገሩ የታመነ ነው፤ ሁሉም ሊቀበሉት የሚገባ ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ መጀመሪያቸው የሆንሁ ኃጥአንን ሊያድን ወደ ዓለም መጥቶአልና። ፲፮ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በእኔ ላይ የትዕግሥቱን ብዛት ይገልጥ ዘንድ፥ የዘለዓለም ሕይወትን ለማግኘት በእርሱ ለሚያምኑም ምሳሌ እሆናቸው ዘንድ ይቅር አለኝ። ፲፯ብቻውን አምላክ ለሚሆን ለማይሞተው፥ ለማይታየውም ለዘለዓለም ንጉሥ ምስጋናና ክብር እስከ ዘለዓለም ድረስ ይሁን፤ አሜን። ፲፰ልጄ ጢሞቴዎስ ሆይ፥ በአንተ ላይ እንደ ተነገረው ትንቢት፥ መልካም ገድልን እንድትጋደል ይህን ትእዛዝ አደራ እልካለሁ። ፲፱ሃይማኖትና መልካም ሕሊና ይኑሩህ፤ ከሃይማኖት የወጡና የጠፉ አሉና። ፳ከእነዚህም ደግሞ እንዲቀጡና ስድብን እንዳይማሩ ለሰይጣን አሳልፌ የሰጠኋቸው ሄሜኔዎስና እለእስክንድሮስ ናቸው።

## ምዕራፍ ፪

### ስለ ጸሎትና ምልጃ

፩ከሁሉ አስቀድሞ ጸሎትና ልመና፥ ምልጃና ምስጋናም ለሰዎች ሁሉ፥ ፪ለነገሥታትና ለመኳንንትም

---

፩ ግሪኩ “እውነተኛ” ይላል።

፪ ግሪኩ “ፍጻሜ የሌለው የትውልዶችን ታሪክ እንዳያመጡ” ይላል።

፫ ግሪኩ “ግብረ ሰዶም ለሚሰሩ” ይላል።

፩፥፪ ሐ.ሥ. ፲፮፥፩። ፩፥፲ ዘፀ. ፳፩፥፲፮። ፩፥፲፫ ሐ.ሥ. ፰፥፫፤ ፱፥፬-፭።

ሁሉ እንዲደረጉ እመክርሃለሁ፤ ይህም ኑሮአችን፦
በቅንነት፥ በጸጥታና በርጋታ እንዲሆን ነው። ፫ይህም
በመድኃኒታችን በእግዚአብሔር ፊት መልካምና የተ
መረጠ ነው። ፬ሰዎች ሁሉ ይድኑ ዘንድ፥ እውነት
ንም ያውቋት ዘንድ እርሱ ይወድዳልና። ፭እግዚአብ
ሔር አንድ ነው፤ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል
ያለው መካከለኛውም አንድ ነው፤ እርሱም ሰው
የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ፮ራሱንም ለሁሉ
ቤዛ አድርጎ ሰጠ፤ በጊዜውም ምስክር ሆነ። ፯እኔም
ሐዋርያና ዐዋጅ ነጋሪ ሆኜ ተሾምሁለት፤ እውነት
ንም እናገራለሁ፤ አልዋሽምም፤ በእምነትና በእው
ነትም ለአሕዛብ መምህር ሆንሁ። ፰እንግዲህ ወን
ዶች በስፍራው ሁሉ የተቀደሱ እጆቻቸውን እያ
ነሡ፥ ያለ ቍጣና ያለ መጠራጠር እንዲጸልዩ እፈ
ቅዳለሁ። ፱እንዲሁም ሴቶች በሚገባ ልብስና በማ
ፈር፥ በማስተዋልም፥ ራሳቸውንም ከዝሙት በማ
ንጻት ለጸሎት ይዘጋጁ፥[፩] በወርቅ ድሪና በዕንቍ፥
ዋጋው በከበረና ባማረ ልብስም አይደለም፤ ፀጕራ
ቸውንም በመሠራት አይደለም። ፲እግዚአብሔርን
ለሚፈሩ ሴቶች እንደሚገባ መልካም በመሥራት
ነው እንጂ። ፲፩ሴትም በጸጥታ ትማር፤ በፍጹም ቅን
ነትም ትታዘዝ። ፲፪ሴት ግን በጸጥታ ትኑር እንጂ፥
እንድታስተምር ወይም በወንድ ላይ እንድትሠለጥን
እንፈቅድም።[፪] ፲፫አዳም በፊት ተፈጥሮአልና፥ ከእር
ሱም በኋላ ሔዋን ተፈጠረች። ፲፬አዳም አልሳተም፤
ነገር ግን ሴቲቱ ተሳሳተች፤ ትእዛዙንም ተላለፈች።
፲፭ነገር ግን በእምነትና በፍቅር፥ በቅድስናም ራሳቸ
ውንም በማንጻት ቢኖሩ በልጆችዋ ትድናለች።

## ምዕራፍ ፫

### የጵጵስና ሹመት ሥርዐት

፩"ጵጵስናን ሊሾም የሚወድ መልካም ሥራን
ወደደ፤" የሚለው ቃል የታመነ ነው። ፪ነገር
ግን ጵጵስናን የሚሾም እንዲህ ሊሆን ይገባ
ዋል፦ የማይነቀፍ፥ አንዲት ሴት ያገባ፥ ትጉህ
ሰው፥ ብልህ፥ እንደሚገባው የሚሠራ፥ እንግዳ
ተቀባይ፥ ራሱን የጠበቀ፥ የሚያስተምርና የሚ
ገሥጽ፥ ፫የማይሰክር፥ ለመማታት እጁን የማ
ያፈጥን፥ ነገር ግን ትዕግሥተኛ፥ የማይጣላና
ገንዘብ የማይወድ፥ ፬የቤቱን አስተዳደር በመል
ካም የሚያስተዳድር፥ በፍጹም ንጽሕና የሚታ
ዘዙ ልጆች ያሉት። ፭ቤቱን ማስተዳደር የማይ
ችል ሰው የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እን
ዴት ያስተዳድራል? ፮እንዳይታበይና እንዳይነ
ቀፍ፥ በሰይጣን ወጥመድም እንዳይያዝ አዲስ
አማኝ አይሁን። ፯በሰይጣን ነቀፋና ወጥመድ
እንዳይወድቅ፥ በውጭ ካሉት ሰዎች መልካም
ምስክር ሊኖረው ይገባዋል።

### የዲቁና ሥርዐት

፰እንዲሁም ዲያቆናት ጭምቶች፥ ቃላቸው
የማይለወጥ፥ የወይን ጠጅ መጠጣትን የማያበዙ፥
ከንቱ ትርፍንም የማይወድዱ ይሁኑ፤ ፱የሃይማኖ
ትንም ምሥጢር በንጹሕ ልብ የሚጠብቁ ሊሆኑ
ይገባል። ፲እነርሱንም አስቀድመው ይፈትኑአ
ቸው፤ ከዚህም በኋላ ያለ ነቀፋ ከሆኑ ያገልግሉ።
፲፩እንዲሁም ሴቶች ራሳቸውን ያንጹ፥ ሥርዐትን
የተማሩ፥ የማያማሉ፥ ብልሆችና ቅኖች፥ በሁ
ሉም የታመኑ ይሁኑ።[፫] ፲፪ዲያቆናትም ልጆቻቸው
ንና የቤታቸውን አስተዳደር በመልካም እየገዙ፥
እያንዳንዳቸው የአንዲት ሴት ባሎች ይሁኑ።
፲፫በመልካም ለሚያገለግሉት ከፍተኛውን ሹመት
ይሰጡአቸው፤ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን ብዙ
ባለሟልነት አለና። ፲፬ወደ አንተ ፈጥኜ እንደም
መጣ ተስፋ አድርጌ ይህን እጽፍልሃለሁ። ፲፭የዘ
ገየሁ እንደ ሆነ ግን የእግዚአብሔርን ቤት እን
ዴት እንደምታስተዳድር ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃ
ለሁ፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ የእውነት ዐምድና መሠ
ረት የሕያው እግዚአብሔር ቤት ናት። ፲፮የዚህ
የመልካም እምልኮ ምሥጢር ታላቅ ነውና። ይኸ
ውም በሥጋ የተገለጠ፥ በመንፈስ የተረዳ፥ ለመ
ላእክት የታየ፥ በአሕዛብ ዘንድ የተሰበከ፥ በዓለም
የታመነ፥ በክብር ያረገ ነው።

## ምዕራፍ ፬

### ስለ ሐሰተኞች የተነገረ ትንቢት

፩መንፈስ፦ በኋላ ዘመን ብዙዎች ሃይማኖታቸ
ውን እንደሚክዱ፥ የሚያስቱ አጋንንትንና የሰይ

---

፩ "ለጸሎት ይዘጋጁ" የሚለው በግሪኩ የለም።

፪ ግሪኩ "አልፈቅድም" ይላል።

፫ ግሪኩ ምዕ. ፫ ቍ. ፲፩ "እንዲሁም ሴቶች ጭምቶች የማያሙ ልከኞች በነገር ሁሉ የታመኑ ሊሆኑ ይገባቸዋል" ይላል።

፪፥፯ ፪ጢሞ. ፩፥፲፩። ፪፥፱ ፩ጴጥ. ፫፥፫። ፪፥፲፫ ዘፍ. ፪፥፯፤ ፳፩-፳፪። ፪፥፲፬ ዘፍ. ፫፥፩-፮።
፫፥፪-፯ ቲቶ ፩፥፯-፱። ፬፥፩ ፪ ጢሞ. ፫፥፩።

ማናትን ትምህርትም እንደሚከተሉ በግልጥ ይናገ
ራል። ፪እነርሱም በግብዝነት ሐሰትን የሚናገሩ፥
በገዛ አሳባቸውም የሚቃጠሉ ናቸው። ፫ጋብቻን
እርም ይላሉ፤ እውነትን የሚያውቁ ምእመናንም
በልተው ያመሰግኑ ዘንድ እግዚአብሔር የፈጠራ
ቸውን ምግቦች ይከለክላሉ። ፬እግዚአብሔር የፈ
ጠረው ፍጥረት ሁሉ መልካም ነውና፤ እያመሰ
ገኑም ቢቀበሉት ምንም የሚጣል የለበትምና።
፭በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት ይቀደሳልና።

## በቃልና በምሳሌነት ስለ ማስተማር

፮ይህንም ለወንድሞችህ አስተምራቸው፤ የሃ
ይማኖትን ቃልና የተከተልኸውን መልካም ትም
ህርት እየመገብሃቸው፥ የተመረጠ የኢየሱስ ክር
ስቶስ አገልጋይ ትሆናለህ። ፯ከረከስ ጨዋታና
ከባልቴቶች ተረት ግን ራቅ፤ ራስህንም ለመ
ልካም እምልኮ አስገዛ። ፰ለሥጋ መገዛት ለጥ
ቂት ዘመን ይጠቅማል፤ መልካም እምልኮ ግን
በሁሉ ግዳጅን ትፈጽማለች፤ በዚህ ዓለምና
በሚመጣውም ዓለም የሕይወት ተስፋ አላት።
፱ነገሩ የታመነ ነው፤ በሁሉም ሊቀበሉት ይገ
ባል። ፲ስለዚህ እንደከማለን፤ እንስደባለንም፤
ሰውን ሁሉ፥ ይልቁንም የሚአምኑትን አዳኝ
በሆነው በሕያው እግዚአብሔር ታምነናልና።
፲፩ይህን እዘዝና አስተምር። ፲፪በቃልና በኑሮ፥
በፍቅርም፥ በእምነትም፥ በንጽሕናም ለሚያምኑት
ምሳሌ ሁን እንጂ ታናሽነትህን ማንም አይናቀው።
፲፫እስክመጣ ድረስ በማንበብና በመምከር፥ በማስ
ተማርና በመጸለይ[፩] ተጠንቀቅ። ፲፬ትንቢት ከመ
ናገር ጋር በጳጳሳት[፪] እጅ መጫን የተሰጠህን በአ
ንተ ላይ ያለውን ጸጋ አታቃልል። ፲፭ፍጹምነትህ
በሁሉ ይታወቅ ዘንድ ይህን አንብብ፤ በዚህም ጸን
ተህ ኑር። ፲፮እንግዲህ ለራስህና ለትምህርትህ ተጠ
ንቀቅ፤ በእነዚህም ጸንተህ ኑር፤ ይህን ብታደርግ
ራስህንም፥ የሚሰሙህንም ታድናለህና።

## ምዕራፍ ፭

## ሽማግሌዎችን ስለ ማክበርና ስለ መታዘዝ።

፩ሽማግሌዎችን አትንቀፍ፤ ነገር ግን ለእነ
ርሱ እንደ አባትህ፥ ለጐበዞቹም እንደ ወንድ
ሞችህ ታዘዝ።[፫] ፪ለባልቴቶችም እንደ እናትህ
ታዘዝ፤ ለወጣቶች ሴቶችም እንደ እኅቶችህ
በፍጹም ንጽሕና ታዘዝ።

## ስለ ልጆችና ባል ስለሌላቸው ሴቶች

፫በእውነት ባልቴቶች የሆኑትን አክብር። ፬ከእ
ነርሱም መካከል ልጅ ወይም የልጅ ልጆች
ያሏት ባልቴት ብትኖር አስቀድሞ ለቤተ ሰዎ
ቻቸው መልካም እምልኮን ያስዩ ዘንድ፥ ለወ
ላጆቻቸውም ብድራትን ይመልሱላቸው ዘንድ
ይማሩ። ይህ በእግዚአብሔር ፊት መልካምና
የተወደደ ነውና። ፭በእውነት ባልቴት የሆነች
ብቻዋን የምትኖር ተስፋዋ እግዚአብሔር ነው፤
ሌሊትና ቀንም በጸሎት ተፀምዳ ትኖራለች።
፮በጨዋታ ተድላ የምታደርግ ግን፥ በሕይወቷ
ሳለች የሞተች ናት። ፯ነውር እንዳይገኝባቸው
ይህን ደግሞ እዘዝ። ፰[፬]ለራሱ ስለ ሆኑት፥
ይልቁንም ስለ ቤተ ሰዎቹ የማያስብ፥ ማንም
ቢሆን ሃይማኖቱን የካደ፥ ከማያምንም ይልቅ
የከፋ ነው።

## ዲያቆናውያትን ስለ መምረጥ

፱ባልቴትን ልትሾም ብትመርጥ ዕድሜዋ
ስድሳ የሆናትን፥ አንድ ባልም ያገባችውን
ምረጥ። ፲በበጎ ምግባር የተመሰከረላት፥ ልጆ
ችዋን በሥርዐት ካሳደገች፥ እንግዳን ከተቀ
በለች፥ የጻድቃንን እግር ካጠበች፤ የተራበ
ውን ካበላች፥ በጎ ምግባርንም ሁሉ ከተከ
ተለች ትመረጥ። ፲፩ባል የሞተባቸውን ቈነ
ጃጅት ሴቶችን ግን በክርስቶስ ላይ እንዳይ
ቀማጠሉ ራቃቸው፤ አትሹማቸውም፤ እነ
ርሱ ወደ ጋብቻ ሊመለሱ ይወዳሉና። ፲፪ፍር
ድም ይጠብቃቸዋል፤ የቀደመችውን እምነታ
ቸውን ክደዋልና። ፲፫ደግሞም መንደር ለመን
ደር እየዞሩ ሥራ ፈትነትንና ስንፍናን ይማ
ራሉ፤ ሥራ መፍታትን ብቻ አይደለም፤ እን
ደገና ወሬንና የኀጢአትን ሥራ ሊያራቡ፥
የሌላውን ነገር ይፈጥራሉ እንጂ። ፲፬እንግ
ዲህ እኔ ቈነጃጅት እንዲያገቡ፥ ልጆችንም
እንዲወልዱ፥ ቤተ ሰዎቻቸውንም እንዲያስ
ተዳድሩ፥ ጠላትም እነርሱን ድል የሚነሣ

---

፩ "በመጸለይ" የሚለው በግሪኩ የለም።

፪ ግሪኩ "ሽማግሌዎች" ይላል።

፫ ግሪኩ "ምከር" ይላል።

፬ ግእዙ "ለቤቱ የማያስብ፥ ዘመዶቹንም ቢጥል ይልቁንም ከሃይማኖት ሰዎች ቢሆኑ ..." ይላል።

፬፥፬ ዘፍ. ፩፥፴፩። ፬፥፯ ፪ጢሞ. ፪፥፲፮፣፳፫። ፭፥፩ ዘሌ. ፲፱፥፴፪። ፭፥፭ ሉቃ. ፪፥፴፯።

በትን እንዳች ምክንያት እንዳያገኝና ራሳ
ቸውን እንዳያስነቅፉ እፈቅዳለሁ። ፲፭ከአ
ሁን በፊት ተመልሰው ሰይጣንን የተከተሉ
አሉና። ፲፮ከምእመናን ወገን ድሆች ባልቴ
ቶች ያሉት ቢኖር ይርዳቸው፤ ቤተ ክርስቲ
ያንም ረዳት የሌላቸውን እውነተኞች ባልቴ
ቶችን ለመርዳት ትችል ዘንድ ሸክም አይ
ሁኑባት።

## ስለ ቀሳውስት ክብር

፲፯በመልካም የሚያስተዳድሩ ቀሳውስት
ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚ
ደክሙ እጥፍ ክብር ይገባቸዋል። ፲፰መጽ
ሐፍ፥ "እህልህን በምታበራይበት ጊዜ በሬ
ውን አፉን አትሰረው፥ ለሚሠራም ደመወዙ
ይገባዋል" ይላልና። ፲፱ሁለት ወይም ሦስት
ምስክሮች ሳይመሰክሩበት በሽማግሌው ላይ
ነገር አትስማ፤ ፳ሌላው ደግሞ ይፈራ ዘንድ
የተሳሳቱትን በሰው ሁሉ ፊት ገሥጻቸው።
፳፩በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ ክርስ
ቶስ፥ በተመረጡ መላእክቱም ፊት አድልዎ
ሳታደርግ ይህን እንድትጠብቅ አዳኝብሃለሁ፤
ከፍርድ በፊትም ሰውን እውነተኛ አታድ
ርገው፤ በአድልዎም ምንም አትሥራ።[፫]
፳፪በማንም ላይ ፈጥነህ እጆችህን አትጫን፤
በሌሎች ኀጢአትም አትተባበር፤ ራስህንም
በንጽሕና ጠብቅ። ፳፫ [፬]ስለ ሆድህ በሽታና ስለ
ዘወትር ደዌህ ጥቂት ወይን ጨምር እንጂ
ውኃ ብቻ አትጠጣ።

፳፬ኀጢአቱ የሚታወቅበት ሰው አለ፤ ወደ
ፍርድም ይቀድመዋል፤ ኀጢአቱም የሚከተ
ለው አለ። ፳፭እንዲሁም በጎ የሚሠራ ይታወ
ቃል፤ ሥራውም ሌላ የሆነ አይደበቅም።

## ምዕራፍ ፮

## ስለ ቤተ ሰብእ አስተዳደር።

፩የእግዚአብሔር ስምና ትምህርቱ እንዳይነ
ቀፉ ከቀንበር በታች ያሉ አገልጋዮች ሁሉ ለጌ
ቶቻቸው ክብር ሁሉ እንደሚገባ ይቍጠሩ።
፪ያመኑ ጌቶች ያሉአቸውም ቢኖሩ አይናቋ
ቸው፤ እነርሱ ወንድሞቻቸው ናቸውና፤ ደግ
ሞም አብዝተው ያገልግሉአቸው፤ በመልካም
ሥራቸው ተቀብለው የሚረዱአቸው የታመ
ኑና የተወደዱ ናቸውና፤ እንደዚህ አስተምርና
ምክር

## ከክሕደትና ገንዘብን ከመውደድ ስለ መራቅ

፫ሌላ ትምህርት የሚያስተምር፥ የጌታችን
የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ወደ ሆነው ወደ ሕይ
ወት ነገር ትምህርትና ወደ መልካም አምልኮ
ትምህርት የማይመለስ ቢኖር፥ ፬እንዲህ ያለው
ሰው ይታበያል፤ አንዳችም አያውቅም፤ ነገር
ግን ምርመራንና በቃል መዋጋትን እንደ በሽ
ተኛ ይናፍቃል፤ ከእነዚህም ቅናትና ክርክር፥
ስድብም፥ ክፉ አሳብም፥ እርስ በርስ መናደ
ድም ይወጣሉ። ፭አእምሮአቸው የጠፋባቸውና
ከእውነት የራቁ፥ መልካም አምልኮን መናገጃ
የሚያደርጉ አሉ፤ ከእነዚህም ራቅ። ፮በቃኝ
ከማለት ጋር እግዚአብሔርን ማምለክ ታላቅ
ረብ ነው። ፯ወደ ዓለም ያመጣነው የለንምና፤
ከእርሱም ልንወስደው የምንችል የለምና።
፰ምግባችንንና ልብሳችንን ካገኘን ይበቃናል።
፱ባለጸጋ ሊሆኑ የሚወዱ ግን በጥፋትና በመፍ
ረስ፥ ሰዎችን በሚያስጥምና በሚያስንፍ፥ በሚ
ጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና፥ በወጥመድም
ይወድቃሉ። ፲ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ
ሥር ነውና፥ ይህንም በመመኘት ተሳስተው
ሃይማኖታቸውን የለወጡ ብዙዎች ናቸውና፥
ለራሳቸውም ብዙ መቅሠፍትን ሸተዋልና።

## ስለ ሃይማኖት መልካም ገድል

፲፩የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ አንተ ግን ከዚህ
ሁሉ ራቅ፤ ጽድቅንና መልካም አምልኮን፥ ሃይማ
ኖትንና ፍቅርን፥ ትዕግሥትንና የዋህነትንም ተከታ
ተል። ፲፪የተጠራህለትንና በብዙ ምስክሮች ፊት በመ
ልካም መታመን የታመንህለትን የዘለዓለምን ሕይ
ወት ለመቀበል መልካሙን የሃይማኖት ገድል ተጋ
ደል። ፲፫ሁሉን በሕይወት በሚጠብቅ በእግዚአብ
ሔር ፊት፥ በጴንጤናዊውም በጲላጦስ ፊት መልካ
ሙን መታመን በመሰከረ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት
አዝዝሃለሁ። ፲፬ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪገለጥ
ድረስ፥ ያለ ነውርና ያለ ሐሜት ሆነህ ይህን ትእዛዝ
ጠብቅ። ፲፭ይህንም ብፁዕና ብቻውን ኀያል የሆነ፥

---

፫ "ከፍርድ በፊትም ሰውን እውነተኛ አታድርገው" የሚለው በግሪኩ የለም።

፬ ግሪኩ "ስለ ሆድህና ስለ ዘወትር በሽታህ ..." ይላል።

፭፥፲፰ ዘዳ. ፳፭፥፬፤ ማቴ. ፲፥፲፤ ሉቃ. ፲፥፯።  ፭፥፲፱ ዘዳ. ፲፯፥፮፤ ፲፱፥፲፭።  ፭፥፳፪ ፪ ዮሐ. ፩፥፲፩።
፮፥፲፫ ዮሐ. ፲፰፥፴፯።  ፮፥፲፭ ዘዳ. ፲፥፲፯፤ ራእ. ፲፯፥፲፬።

የነገሥታት ንጉሥ፥ የጌቶች ጌታ በጊዜው ይገልጠ
ዋል። ፲፮እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀር
በው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ አንድ ሰው እንኳ
አላየውም፤ ሊያየውም አይቻለውም፤ ለእርሱ ክብ
ርና የዘለዓለም ኀይል ይሁን፤ አሜን።

## ለባለጸጎች የተሰጠ ትእዛዝ

፲፯የዚህን ዓለም ባለጸጎችም እንዳይታበዩ፥ ደስ
እንዲለንም በባለጸግነቱ ብዛት ሁሉን አብዝቶ
በሚሰጠን በሕያው እግዚአብሔር እንጂ በሚ
ያልፍ ባለጸግነታቸው እንዳይታመኑ እዘዛቸው።
፲፰በጎ ሥራን እንዲሠሩ፥ በበጎ ሥራም ባለጸጎች
እንዲሆኑ፥ ሊረዱና ሊያካፍሉም የተዘጋጁ እን
ዲሆኑ ምከራቸው። ፲፱በሚመጣውም ዓለም እው
ነተኛውን ሕይወት ለማግኘት ለራሳቸው መል
ካም መሠረት የሚሆንላቸውን መዝገብ እንዲሰበ
ስቡ ምከራቸው።

፳ጢሞቴዎስ ሆይ፥ የተሰጠህን አደራ
ጠብቅ፤ ከንቱ ነገር የሚያመጡትንና እው
ነትን በሐሰት የሚያርቁ ርኩሳንንም ተለያ
ቸው።[፩] ፳፩እነርሱ በሃይማኖት ከሚገኘው
ተስፋ ወጥተዋልና፤ ጸጋ ከአንተ ጋር ይሁን፤
አሜን።

በሎዶቅያ ተጽፎ በቲቶ እጅ ወደ ጢሞቴ
ዎስ የተላከ መጀመሪያዉ መልእክት ተፈጸመ።
አሜን።

---

፩ ግሪኩ "... ክርኩስና ከከንቱ ነገር፥ በሐሰትም ዕውቀት ከሚባለው ክርክር ራቅ" ይላል።

፮፥፲፮ ዘፀ. ፴፫፥፳። ፮፥፳ ፪ ጢሞ. ፩፥፲፬። ፮፥፳፩ ፪ ጢሞ. ፪፥፲፰።

# ሁለተኛዉ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ጢሞቴዎስ

## ምዕራፍ ፩

፩ በእግዚአብሔር ፈቃድ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በሚሆን በሕይወት ተስፋ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ከጳውሎስ፦ ፪ ለምወድህ ልጄ ለጢሞቴዎስ፥ ከአባታችን ከእግዚአብሔር፥ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስም ጸጋና ምሕረት፥ ሰላም ለአንተ ይሁን። ፫ ከአባቶቼ ጀምሮ በንጹሕ ልቡና የማመልከውን እርሱን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። ሌሊትና ቀንም በጸሎቴ ዘወትር አስብሃለሁ። ፬ እንባህን አስባለሁ፤ ደስ ይለኝም ዘንድ ላይህ እናፍቃለሁ። ፭ በእናትህ በኤውንቄ፥ በአያትህም በሎይድ ላይ ያደረችውን፥ ጥርጥር የሌለባትን ሃይማኖትህን አስባለሁ፤ በአንተም ላይ ጸንታ እንደምትኖር አተማመናለሁ። ፮ ስለዚህም ምክንያት፥ እጄን በአንተ ላይ በመጫኔ ያገኘኸው የእግዚአብሔር ጸጋ ይታደስልህ ዘንድ አስብሃለሁ። ፯ እግዚአብሔር የኀይልና የንጽሕና፥ የፍቅርና የጥበብ መንፈስን እንጂ የፍርሀት መንፈስን አልሰጠንምና።

፰ እንግዲህስ ለጌታችን ለመመስከር አትፈር፤ እኔንም እስረኛውን አታሳፍረኝ፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ኀይል ወንጌልን ለማስተማር መከራን ተቀበል። ፱ ያዳነን፥ በቅዱስ አጠራሩም የጠራን እርሱ ነውና፤ ዓለም ሳይፈጠር በኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰጠን እንደ ፈቃዱና እንደ ጸጋው እንጂ እንደ ሥራችንም አይደለም። ፲ ይህም ሞትን በሻረው፥ ሕይወትንም በገለጣት፥ በወንጌሉም ትምህርት ጥፋትን ባራቀ በጌታችንና በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ዛሬ ተገለጠ። ፲፩ ለእርሱም እኔ ሐዋርያና ዐዋጅ ነጋሪ፥ ለአሕዛብም መምህር ሆኜ ተሾምሁለት። ፲፪ ስለ እርሱም መከራ እቀበላለሁ፤ እኔም በእርሱ አምኜ አላፍርም፤ ያመንሁትን አውቃለሁና፤ እስከዚያች ቀን ድረስም አደራ የሰጠሁትን[፩] ሊጠብቅልኝ እንደሚችል አምናለሁና። ፲፫ በኢየሱስ ክርስቶስ ባለ እምነትና ፍቅር፥ ከእኔ ዘንድ የሰማኸውያ የሕይወት ቃልም ምሳሌ ይሁንልህ።

፲፬ በእኛ ላይ ባደረው በመንፈስ ቅዱስ መልካሙን አደራህን ጠብቅ። ፲፭ በእስያ ያሉ ሁሉ እንደ ከዱኝ ይህን ታውቃለህ፤ ከእነርሱም እነ ፊሎጎስና እነ ሄርሞጌኔስ[፪] ናቸው። ፲፮ እግዚአብሔር ለሄኔሴፎሩ ቤት ይቅርታውን ይስጠው፤ ብዙ አሳርፎኛልና፤ በእስራቴም አላፈረምና። ፲፯ ወደ ሮሜ በደረሰ ጊዜም ፈጥኖ ፈለገኝ፤ ታስሬም አገኘኝ።[፫] ፲፰ በዚያችም ቀን በጌታችን ፊት ይቅርታን እንዲያገኝ እግዚአብሔር ይስጠው። በኤፌሶንም እንዳገለገለኝ አንተ ራስህ መልካም አድርገህ ታውቃለህ።

## ምዕራፍ ፪

ለኢየሱስ ክርስቶስ መልካም አርበኛ ስለ መሆን

፩ ልጄ ሆይ፥ አንተም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ በርታ። ፪ በብዙ ምስክሮች ፊት ከእኔ የሰማኸውን ትምህርት ለሌሎች ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች እርሱን አስተምራቸው።[፬] ፫ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደሚያገለግል

---

፩ አንዳንድ የግእዝ ዘርዕ "አደራ የሰጠኝን ..." ይላል።

፪ ግሪኩ "ፊጌሎስና እነ አርሞጌኔስ" ይላል።

፫ "ታስሬም አገኘኝ" የሚለው በግሪኩ የለም።

፬ ግሪኩ "አደራ ስጥ" ይላል።

፩፥፪ ሐ.ሥ. ፲፮፥፩። ፩፥፭ ሐ.ሥ. ፲፮፥፩። ፩፥፲፩ ፩ጢሞ. ፪፥፯።

በጎ አርበኛ ሆነህ መከራ ተቀበል። ፬ወደ ሰልፍ
የሚሄድ፥ አለቃውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ነው
እንጂ የዚህን ዓለም ኑሮ እያሰብምና። ፭የሚ
ታገልም ቢሆን እንደ ሕጉ ካልታገለ አክሊልን
አያገኝም። ፮የሚደክም አራሽም አስቀድሞ ፍሬ
ውን ሊያገኝ ግድ ነው። ፯ያልሁህን አስተውል፤
እግዚአብሔርም በሁሉ ነገር ጥበብን ይሰጥህ።
፰በወንጌል እንደምሰብከው፥ ከሙታን ተለ
ይቶ የተነሣውን ከዳዊት ዘር የሆነውን ኢየሱስ
ክርስቶስን አስበው። ፱ስለ እርሱም እንደ ወንጀ
ለኛ እስክታሰር ድረስ መከራ እቀበላለሁ፤ የእ
ግዚአብሔር ቃል ግን አይታሰርም። ፲ስለዚህ
እነርሱ ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን ሕይ
ወትና የዘለዓለም ክብር በስማያት ያገኙ ዘንድ፥
ስለ ተመረጡት ሰዎች በሁሉ ነገር እታገሣ
ለሁ። ፲፩ነገሩ እውነት ነው፤ ከእርሱ ጋር ከሞ
ትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንኖራለን።
፲፪ብንታገሥም ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሣለን፤
ብንክደው ግን እርሱም ይክደናል። ፲፫ባናም
ነውም እርሱ የታመነ ሆኖ ይኖራል፤ ራሱን
መካድ አይቻለውምና።
፲፬እንግዲህ ይህን አሳስባቸው፤ በቃልም እን
ዳይጣሉ፥ በእግዚአብሔር ፊት ምከራቸው፤
ይህ ምንም የማይጠቅም፥ የሚሰሙትንም የሚ
ያፈርስ ነውና። ፲፭የእግዚአብሔርን ቃል[፩] በእ
ውነት አቃንቶ ሲያስተምር እንደማያፍር ሠራ
ተኛ ሆነህ፥ ራስህን የተመረጠ አድርገህ ለእ
ግዚአብሔር ታቀርብ ዘንድ ትጋ። ፲፮ነገር ግን
ጥቅም የሌለውን የርኩሳንን ነገር ተወው፤ ኀጢ
አታቸውን ያስፋፉአታልና። ፲፯ነገራቸውም በብ
ዙዎች ላይ እንደሚታይና እንደሚሰፋ ቍስል
ነው፤ እነርሱም ሄሜኔዎስና ፊሊጦስ ናቸው።
፲፰እነዚህም፡- ከእውነት የወጡና ትንሣኤ ምው
ታን ፈጽሞ ተደርጎአል የሚሉ፥ የብዙ ሰዎች
ንም ሃይማኖት የሚለውጡ ናቸው። ፲፱"እግዚአ
ብሔር ወገኖቹን ያውቃቸዋል፤ የእግዚአብሔር
ንም ስም የሚጠራ ሁሉ ከክፉ ነገር ይርቃል።"
የሚለው ይህ ማሕተም ያለበት የእግዚአብሔር
መሠረት ጸንቶ ይቆማል።
፳በታላቅ ቤት ውስጥም ከወርቅና ከብር የተ
ሠራ ዕቃ ብቻ አይኖርም፤ ነገር ግን ከዕን
ጨትና ከሸክላም የተሠራ ዕቃ ይኖራል፤ ለክ
ብር የሚሆን አለ፤ ለውርደትም የሚሆን አለ።
፳፩ከዚህም ክፉ ነገር ራሱን ያነጻ ሰው ቢኖር
የተቀደሰና ጌታውን ለማገልገል የሚጠቅም፥
ለበጎ ምግባርም ሁሉ የተገባ የክብር ዕቃ ይሆ
ናል። ፳፪እንግዲህ ከጕልምስና ምኞት ራቅ፤ እግ
ዚአብሔርንም በንጹሕ ልብ ከሚጠሩት ሁሉ
ጋር ጽድቅን፥ሃይማኖትንም፥ ፍቅርንም፥ ሰላም
ንም ተከተል። ፳፫ጠብን እንደሚያመጣ ዐውቀህ
ከስንፎችና ካልተማሩ ሰዎች ምርመራ ራቅ።
፳፬የእግዚእብሔር አገልጋይ ግን አይጣላም፤
ነገር ግን ከሁሉ ጋር እንደ ሕፃን የዋህ፥ ለማ
ስተማር የሚበቃ፥ ክፉ ነገርንም ሁሉ የሚታ
ገሥ ይሆናል። ፳፭እውነትን እንዲያውቁ፥ ምና
ልባት እግዚእብሔር ንስሓን ይሰጣቸው እንደ
ሆነ የሚጣሉትን በቅንነት ይመክራል። ፳፮ከሰ
ይጣን ወጥመድ እንዲድኑ ፈቃዱን ለመከተል
ፈጽሞ አጥምዶአቸዋልና።

## ምዕራፍ ፫

### በኋለኛው ዘመን ስለሚደርሰው ክፉ ነገር

፩ነገር ግን በኋላ ዘመን ክፉ ጊዜ እንደሚመጣ
ይህን ዕወቅ። ፪ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ፥ ገን
ዘብንም የሚወዱ፥ ቀባጣሪዎች፥ ትምክሕተ
ኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻ
ቸው የማይታዘዙ፥ ምስጋና የሌላቸው፥ ከጽድ
ቅም የወጡ ይሆናሉ። ፫ፍቅር የሌላቸው፥ ዕር
ቅን የማይሰሙ፥ ሐሜተኞች፥ ራሳቸውን የማ
ይገዙ፥ ጨካኞች፥ መልካም የሆነውንም የሚ
ጠሉ ይሆናሉ። ፬ከዳተኞች፥ ችኩሎች፥ በትዕ
ቢት የተነፉ፥ ከእግዚእብሔር ይልቅ ተድላን
የሚመርጡ ይሆናሉ። ፭የእምልኮት መልክ አላ
ቸው፤ ኀይሉን ግን ይክዱታል፤ እንደ እነዚህ
ያሉትን ራቃቸው። ፮እነዚህ በየሰዉ ቤት የሚ
ገቡና በኀጢአት የተተበተቡትን ሴቶች የሚ
ማርኩ፥ ወደ ብዙ ምኞትም የሚደርሱ ናቸ
ውና፤ ፯ዘወትር ይማራሉ፤ ነገር ግን እውነ
ትን ከቶ አያውቋትም። ፰ኢያኔስና ኢያንበሬስ
ሙሴን እንደ ተቃወሙት እነዚህም እውነትን
ይቃውሙአታል፤ እእምሮአቸውም የጠፋባቸ
ውና ከእምነት የወጡ ሰዎች ናቸው። ፱ነገር
ግን ከፍ ከፍ አይሉም፤ የእነዚያ ስንፍና ደግሞ
እንደ ተገለጠ ስንፍናቸው በዝታ ለሁሉ ተገ
ልጣለችና።

---

፩ ግሪኩ "የእውነትን ቃል" ይላል።
፪፥፲፪ ማቴ. ፲፥፴፫፤ ሉቃ. ፲፪፥፱።   ፪፥፲፱ ዘኍ. ፲፮፥፭።   ፪፥፳ ሮሜ. ፱፥፳፩።   ፪፥፳፪ ፩ ጢሞ. ፮፥፲፩።
፫፥፰ ዘፀ. ፯፥፲፩።

## መምህራንን ስለ መከተል

፲አንተ ግን ትምህርቴንና ግብሬን፥ አሳቤ
ንም፥ እምነቴንም፥ ትዕግሥቴንም፥ ፍቅሬ
ንም፥ መጽናናቴንም ተከተልህ፤ ፲፩ስደቴንና፥
መከራዬንም ተከተልህ፤ በአንጾኪያና በኢቆን
ዮን፥ በልስጥራንም ያገኘኝን የታገሥሁትንም
ስደት ታውቃለህ፤ ከሁሉም እግዚአብሔር አዳ
ነኝ። ፲፪ኢየሱስ ክርስቶስንም በማምለክ ሊኖሩ
የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ። ፲፫ነገር ግን ክፉ
ዎች ሰዎችና አታላዮች በክፋት ላይ ክፋትን
እየጨመሩ ይሄዳሉ፤ ራሳቸው ይስታሉ፤ ሌላ
ውንም ያስታሉ። ፲፬አንተ ግን በተማርህበትና
በተረዳህበት ጸንተህ ኑር፤ ከማን እንደ ተማ
ርኸው ታውቃለህና። ፲፭ከሕፃንነትህም ጀምረህ
ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን መዳን የሚገኝበ
ትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻ
ሕፍትን ዐውቀሃል። ፲፮በእግዚአብሔር መን
ፈስ የተጻፈ መጽሐፍ ሁሉ ለፍጹም ትምህ
ርትና ለተግሣጽ፥ ልብንም ለማቅናት በጽድ
ቅም ላለው ጥበብ ይጠቅማል። ፲፯የእግዚአብ
ሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ምግባር ሁሉ የተዘ
ጋጀ ይሆን ዘንድ።

## ምዕራፍ ፬

፩አሁንም በእግዚአብሔር ፊትና በመንግሥቱ
በሚመጣበት ጊዜ፥ በሕያዋንና በሙታን ይፈ
ርድ ዘንድ ባለው በጌታችን በኢየሱስ ክርስ
ቶስ ፊት እመክርሃለሁ። ፪በዝግታ ቆመህ በጊ
ዜውም ያለጊዜውም ቃሉን ስበክ፤ በሁሉም
እየታገሥህና እያስተማርህ፥ ገሥጽ፤ ዝለፍ፤
ፈጽመህም አጽናና። ፫ሕይወት የሚገኝበትን
ትምህርት የማይታገሡበት ጊዜ ይመጣልና፤
ነገር ግን በጆሮአቸው ቀባዛነት እንደ ገዛ ምኞ
ታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያመጣሉ።
፬እውነትንም ከመስማት ጆሮአቸውን ይመል
ሳሉ፤ ወደ ተረትም ይመለሳሉ። ፭አንተ ግን
ንቃ፤ በሁሉም ብልህ ሁን፤[ሀ] መከራ ተቀ
በል፤ የወንጌላዊ ሥራን ሥራ፤ መልእክትህ
ንም ፈጽም።

## የቅዱስ ጳውሎስ የገድሉ ፍጻሜ

፮እኔ ፈጽሜ ግዳጄን ጨርሻለሁ፤ የማርፍ
በት ዕድሜዬም ደርሶአል። ፯መልካሙን ገድል
ተጋድያለሁ፤ ሩጫዬንም ጨርሻለሁ፤ ሃይማኖ
ቴንም ጠብቄአለሁ። ፰እንግዲህስ የጽድቅ አክ
ሊል ይቆየኛል፤ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው
እግዚአብሔር በዚያ ቀን ለእኔ ያስረክባል፤ ደግ
ሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ
ብቻ አይደለም።

## ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ስለመጥራቱ

፱በቶሎ ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ ተፋጠን።
፲ዴማስ ይህን የዛሬውን ዓለም ወድዶ እኔን
ተወኝ፤ ወደ ተሰሎንቄም ሄደ፤ ቄርቂስም
ወደ ገላትያ፥ ቲቶም ወደ ድልማጥያ ሄዱ።
፲፩ሉቃስ ብቻ ከእኔ ጋር ነው፤ ማርቆስን ከአ
ንተ ጋር አምጣው፤ እርሱ ለመልእክት ይጠ
ቅመኛልና። ፲፪ቲኪቆስንም ወደ ኤፌሶን ላክ
ሁት። ፲፫ስትመጣም በጢሮአስ በአክርጳ ዘንድ
የተውሁትን በርኖሱንና መጻሕፍቱን፥ ይልቁ
ንም ብራናውን አምጣልኝ። ፲፬እንጥረኛው እለ
እስክንድሮስ በብዙ አሠቃየኝ፤ ነገር ግን እግ
ዚአብሔር እንደ ሥራው ይከፈለው። ፲፭አን
ተም ከእርሱ ተጠበቅ፤ ትምህርታችንን እጅግ
ተቃውሞአልና። ፲፮በመጀመሪያ ክርክሬ ሁሉም
ተዉኝ እንጂ ከእኔ ጋር የተባበረ የለም፤ ይህ
ንም እግዚአብሔር ይቅር ይበላቸው። ፲፯የስብ
ከቱ ሥራ በእኔ እንዲፈጸም፥ አሕዛብም ሁሉ
እንዲሰሙት፥ እግዚአብሔር ቆመልኝ፤ አጸና
ኝም፤ ከአንበሳ አፍም ዳንሁ። ፲፰እግዚአብሔ
ርም ከክፉ ነገር ሁሉ ያድነኛል፤ ለሰማያዊ
ውም መንግሥት ይጠብቀኛል፤ ለእርሱ ከዘለ
ዓለም እስከ ዘለዓለም ክብር ይሁን።

## የመልእክቱ ፍጻሜ

፲፱ጵርስቅላንና አቂላን፥ የሄኔሲፎሩንም ቤተ
ሰብእ ሰላም በል። ፳አርስጦስ በቆሮንቶስ ቀረ፤
ጥሮፊሞስን ግን ታሞ በሚሊጡ ተውሁት።
፳፩ከክረምት በፊት እንድትመጣ ፍጠን፤ ኤው

---

ሀ “በሁሉም ብልህ ሁን” የሚለው በግሪኩ የለም።

፫፥፲፩ ሐ.ሥ. ፲፫፥፲፬-፶፪፤ ፲፬፥፩-፯፤ ፲፱-፳። ፫፥፲፪ ማቴ. ፲፮፥፳፬። ፫፥፲፭ መዝ. ፻፲፰፥፺፱።
፫፥፲፮ ሮሜ. ፲፭፥፬፤ ፪ ጴጥ. ፩፥፳-፳፩። ፬፥፲ ቆላ. ፬፥፲፬፤ ፊልሞና ፳፬፥ ፪ቆሮ. ፰፥፳፫፤ ገላ. ፪፥፫፤ ቲቶ ፩፥፬።
፬፥፲፩ ቆላ. ፬፥፲፬፤ ፊልሞና ፳፬፤ ሐ.ሥ. ፲፪፥፲፪፤ ፳፭፤ ፲፫፥፲፫፤ ፲፭፥፴፯-፴፱፤ ቆላ. ፬፥፲። ፬፥፲፫ ሐ.ሥ. ፳፥፮።
፬፥፲፬ ፩ጢሞ. ፩፥፳፤ መዝ. ፷፩፥፲፪፤ ሮም ፪፥፮። ፬፥፲፱ ሐ.ሥ. ፲፰፥፪፤ ፪ጢሞ. ፩፥፲፮-፲፯።
፬፥፳ ሐ.ሥ. ፲፱፥፳፪፤ ሮም ፲፮፥፳፫፤ ሐ.ሥ. ፳፥፬፤ ፳፩፥፳፱።

ግሎስና ጴዴስ፥ ሊኖስም፥ ቀላውድያም ወንድ
ሞቻችንም ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡልሃል። [፳፪] ጌታ
ችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመንፈስህ ጋር ይሁን፤
ጸጋ ከአንተ ጋር ይሁን፤ [፩] አሜን።

ወደ ጢሞቴዎስ የተላከ ሁለተኛው መልእክት ተፈጸመ፤ በሮሜ ተጽፎ፥ በአንክሮሎስ እጅ ተላከ።

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። አሜን።

---

፩ አንዳንድ ዘርዕ "ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን" ይላል።

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ቲቶ

## ምዕራፍ ፩

፩የእግዚአብሔር ባሪያና የኢየሱስ ክርስቶስ
ሐዋርያ ከሆነ ከጳውሎስ፥ እንደ እግዚአብሔር
ምርጦች እምነት፥ እንደ መልካም አምልኮ
ያለች እውነትንም በማወቅ፥ ፪ሐሰት የማይና
ገር እግዚአብሔር ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ በሰ
ጠው የዘለዓለም ሕይወት ተስፋ፥ ፫በዘመኑም
በመድኀኒታችን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ለእኔ
አደራ በተሰጠኝ ስብከት ቃሉን የገለጠ፥ ፬በፍ
ቅርና በሃይማኖት ለምወድድህ ልጄ ለቲቶ፥
ከአባታችን ከእግዚአብሔር፥ ከጌታችንና ከመ
ድኀኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስም ጸጋና ምሕ
ረት፥ ሰላምም ለአንተ ይሁን።

### ስለ ቅስና ሹመት

፭ስለዚህ ምክንያት የቀረውን እንድታደራጅ፥
በየከተማውም እኔ አንተን እንደ አዘዝሁህ ቀሳ
ውስትን[፩] እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ። ፮የአ
ንዲት ሚስት ባልና የማይነቀፍ፥ የሚያምኑ ልጆ
ችም ያሉት፥ ስለ መዳራት፥ ወይም ስለ አለመ
ታዘዝ የማይከሰስ ማንም ቢኖር ሹመው። ፯ጳጳስ
እንደ እግዚአብሔር መጋቢ የማይነቀፍ ሊሆን
ይገባዋልና፤ የማይኮራ፥ ቍጡ ያይደለ፥ የማይሰ
ክር፥ የማይጨቃጨቅ፥ ከንቱ ረብን የማይወድ፥
፰እንግዳ የሚቀበል፥ ምግባሩ መልካም የሆነ፥
ራሱን የጠበቀ፥ ጻድቅ፥ ቅዱስ፥ ራሱን የሚገዛ
ይሁን። ፱ሕይወት በሚገኝበት ትምህርት ደግሞ
ሊመክር፥ ተቃዋሚዎቹንም ሊገሥጽ ይችል
ዘንድ፥ እንደ ተማረው በታመነ ቃል ይጽና።
፲የማይታዘዙ፥ ነገራቸው ከንቱ የሆነ፥ ማስተ
ዋል የጕደላቸውንም[፪] የሚያታልሉ፥ ይልቁንም
ከአይሁድ ወገን የሚሆኑ ብዙ ናቸውና። ፲፩እን
ዚህ ስለ ነውረኛ ረብ የማይገባውን እያስተማሩ፥
ቤቶችን ሁሉ ስለሚገለብጡ አፋቸውን መዝ
ጋት ይገባል። ፲፪የገዛ ራሳቸው ነቢይ የሆነ ከእ
ነርሱ አንዱ፥ "የቀርጤስ ሰዎች ግብዞች፥ ዘወ
ትር ውሸተኞችና ከፉዎች፥ አውሬዎችና፥ የመ
ሃን ማኅፀን ናቸው፤" ብሎአል። ይህም ምስክር
ነት በእነርሱ ላይ የታመነ ነው። ፲፫ስለዚህም ሃይ
ማኖትን እንዲረዱ[፫] በቍርጥ ገሥጻቸው። ፲፬የአ
ይሁድን ተረትና እውነትን የሚለውጡ የሰዎችን
ትእዛዝ እንዳያመጡ ገሥጻቸው። ፲፭ሁሉ ለንጹ
ሓን ንጹሕ ነው፥ ለማያምኑና ለርኩሳን ግን
ምንም ንጹሕ የሆነ የለም፤ አእምሮአቸውም፥
ሕሊናቸውም የረከሰ ነውና። ፲፮እግዚአብሔርን
እንደሚያውቁት በግልጥ ይናገራሉ፤ በሥራቸው
ግን ይክዱታል፤ እነርሱም ርኩሳንና የማይታ
ዘዙ፥ በበጎ ሥራም ሁሉ የተናቁ ናቸው።

## ምዕራፍ ፪

### ስለ ክርስቲያን ኑሮ ሥርዐት

፩አንተ ግን ለሕይወት ትምህርት የሚገባውን
ተናገር። ፪ሽማግሌዎችም ከዝሙት የነጹ፥ የነ
ቁና ብልሆች ይሆኑ ዘንድ፥ በሃይማኖት እንዳ
ይጠራጠሩ፥ እንዲፋቀሩና አስተውለው እንዲ
ታገሡ ተናገር። ፫ባልቴቶችም እንዲሁ በጠባያ
ቸው የተቀደሱ፥ የማያሙና ለመጠጥ የማይገዙ
ይሁኑ፤ በጎ የሆነውንም ትምህርት ራሳቸውን
ያነጹ ዘንድ ለሴቶች ያስተምሩ።[፬] ፬ወጣቶች ሴቶ
ችንም ባሎቻቸውንና ልጆቻቸውን እንዲወዱ

---

፩ ግሪኩ "ሽማግሌዎችን" ይላል።

፪ "ማስተዋል የጕደላቸውንም ..." የሚለው በግሪኩ የለም።

፫ ግሪኩ "በሃይማኖት ጤናሞች እንዲሆኑ ..." ይላል።

፬ "ራሳቸውን ያነጹ ዘንድ ለሴቶች ያስተምሩ" የሚለው በግሪኩ የለም።

፩፥፩ ፪ቆሮ. ፰፥፳፫፤ ገላ. ፪፥፫፤ ፪ጢሞ. ፬፥፲። ፩፥፮-፱ ፩ጢሞ. ፫፥፪-፯። ፩፥፲፭ ሮሜ. ፲፬፥፳።

ያስተምሩ፤ ፭በእነርሱ ምክንያት አንድ ሰው እን
ኳን የእግዚአብሔርን ቃል እንዳይነቅፍ ራሳቸ
ውን የሚገዙ ንጹሖች እንዲሆኑ፥ በጎውን እንዲ
ሠሩ፥ ጠባያቸውንና የቤታቸውን ሥርዐት እን
ዲያሳምሩ፥ ለባሎቻቸውም እንዲታዘዙ ይምከሩ
አቸው። ፮ጎበዞቹንም ስውነታቸውን እንዲጠብቁ
ብልሆችም እንዲሆኑ[፩] ምከራቸው። ፯በበጎ ምግባ
ርም ስሁሉ አርአያና ምሳሌ ሁናቸው። ፰የሚቃ
ወም ሰው በእኛ ላይ የሚናገረውን መጥፎ ነገር
ሲያጣ እንዲያፍር አነጋገርህና ትምህርትህ አንድ
ሰው እንኳ በማይነቀው፥ ነውር በሌለበትና ሥር
ዐት ባለው አነጋገር በንጹሕ ይሁን። ፱አገልጋዮ
ችም ስጌቶቻቸው ይታዘዙ፤ በሁሉም ደስ ያሰ
ኙአቸው፤ በሁሉም አይጨቃጨቁ። ፲አይስረቁ፤
ነገር ግን መድኀኒታችን እግዚአብሔር ያስተማ
ረውን ትምህርት በቦታው ሁሉ ያመሰግኑ ዘንድ
በንጹሕ ሥራቸው እምነታቸውን ይግለጡ።

፲፩የሚያድነው የእግዚአብሔር ጸጋ በስው
ሁሉ ዘንድ ታውቆአልና። ፲፪እርስዋም ከኀጢ
አትና ከዓለም ፍትወት እንስይ ዘንድ፥ በዚህ
ዓስምም በጽድቅ፥ በንጽሕናና በፍቅር እንኖር
ዘንድ ታስተምረናለች። ፲፫የተመሰገነውን ተስፋ
የታላቁን የአምላካችንን የመድኀኒታችን የኢ
የሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥
፲፬ከኀጢአት ይቤዠን ዘንድ፥ በበጎ ምግባር
የሚፎካከር አዲስ ሕዝብንም ለእርሱ ይመርጥ
ዘንድ ስለ እኛ ራሱን አሳልፎ የሰጠ። ፲፭ስሁሉ
ራስህን ዝቅ እያደረግህ[፪] ይህን ስሁሉ ምከርና
አስተምር፤ ገሥጽም፤ የሚያስትህም አይኑር።

## ምዕራፍ ፫

### ስለ መምህራን ሥራ

፩ለገዦችና ለባለሥልጣኖች የሚገዙና የሚ
ታዘዙ፥ ሰበጎ ሥራም ሁሉ የተዘጋጁ፥ ፪ማን
ንም የማይሳደቡ፥ የማይከራከሩ፥ ገሮች፥
ለሰው ሁሉ የዋሃትን ሁሉ የሚያሳዩ እንዲ
ሆኑ አሳስባቸው። ፫እኛም ደግሞ አስቀድመን
የማናስተውል ነበርንና፥ የማንታዘዝ፥ የምን
ስት፥ ለምኞትና ስልዩ ልዩ ተድላ እንደ ባሪ
ያዎች የምንገዛ፥ በክፋትና በምቀኝነት የም
ንኖር፥ የተጠላን፥ እርስ በርሳችንም የምንጠ
ላላ ነበርንና። ፬ነገር ግን የመድኀኒታችን የእ
ግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተ
ገለጠ ጊዜ፥ ፭ዳግም ልደትንና፥ በመንፈስ
ቅዱስ መታደስን በሚያሰጥ ጥምቀት በምሕ
ረቱ አዳነን እንጂ በጽድቅ ሥራችን አይደ
ለም። ፮ይኸውም መድኀኒታችን ኢየሱስ ክር
ስቶስ ስስ ካሰልን በለጋስነቱ በእኛ ላይ ያሳደ
ረው ነው። ፯በቸርነቱ እንጸድቅ ዘንድ፥ የዘለ
ዓስምን የሕይወት ተስፋም እንወርስ ዘንድ።
፰ነገሩ እውነት ነው፤ ስስዚህም እሻስሁ፤ በእ
ግዚአብሔር የሚያምኑ ሰዎች በመልካም ምግ
ባር ሁሉ መረዳዳትን እንዲያስቡ ታጸናቸው
ዘንድ እወዳለሁ፤ ሰውንም የሚጠቅመው በጎ
ነገር ይህ ነው። ፱ፈጥረው ከሚናገሩት የጠብና
የስንፍና ነገር፥ ከተረትና ከዋዛ ነገር ራቅ፤
ከንቱና የማይጠቅሙ ናቸውና። ፲ከዶ የሚያ
ስከድን ሰው አንድ ጊዜና ሁለት ጊዜ ከመከ
ርኸውና እንቢ ካለ ተወው። ፲፩እንዲህ ያለው
ሰው የሚያሳስትና የሚያስከድ መናፍቅ እንደ
ሆነ፥ በራሱም ላይ ፍርድን እንደሚያመጣ
አስታውቅበት።

### የመልእክት ፍጻሜ

፲፪አርጢሞንን ወይም ቲኪቆስን ወደ አንተ
የላክሁት እንደ ሆነ፥ ፈጥነህ ወደ እኔ ወደ
ኒቆጵልዮን ከተማ ና፤ በዚያ ልከርም ቈርጫ
ስሁና። ፲፫የሀገሩን ጸሓፊ[፫] ዜማስን፥ አጵሎስ
ንም በምንም እንዳይቸገሩ በጕዞአቸው ተግተህ
ርዳቸው። ፲፬ወገኖቻችንም ፍሬ ቢሶች እንዳይ
ሆኑ፥ በሚፈለገውም ሥራ ጸንተው እንዲገኙ
በጎ ምግባርን ይማሩ።

፲፭ከእኔ ጋር ያሉት ሁሉ ሰላም ብለውሃል፤
በሃይማኖት የሚወደንን ሁሉ ሰላም በል፤ ጸጋ
ከሁላችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን።

ወደ ቲቶ የተላከች መልእክት ተፈጸመች፤
በኒቆጵልዮን ከተማ ተጻፈች፤ በደቀ መዝሙሩ
በአርጣማ እጅ ተላከች።

ስእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። አሜን።

---

፩ "ብልሆችም እንዲሆኑ" የሚለው በግሪኩ የለም።
፪ "ስሁሉ ራስህን ዝቅ እያደረግህ" የሚለው በግሪኩ የለም።
፫ ግሪኩ "ሕግ አዋቂ" ይላል።
፪፥፲፬ መዝ. ፻፴፱፥፰፤ ዘፀ. ፲፱፥፭፤ ዘዳ. ፬፥፳፤ ፯፥፮፤ ፲፬፥፪፤ ፩ጴጥ. ፪፥፱።
፫፥፲፪ ሐ.ሥ. ፳፥፬፤ ኤፌ. ፮፥፳፩-፳፪፤ ቆላ. ፬፥፯-፱፤ ፪ጢሞ. ፬፥፲፪። ፫፥፲፫ ሐ.ሥ. ፲፰፥፳፬፤ ፩ቆሮ. ፲፮፥፲፪።

# የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልሞና

## የምልጃና የምስጋና መልእክት

፩ከኢየሱስ ክርስቶስ እስረኛ ከጳውሎስ፥ ከወንድማችንም ከጢሞቴዎስ፥ በሥራ ስሚተባበረን ስምንወደው ለፊልሞና፥ ፪ለእኅታችን ለአፍብያ፥ ከእኛም ጋር አብሮ ለሚጋደል ለአክርጳ፥[፩] በቤትህም ላለች ቤተ ክርስቲያን፥ ፫ከአባታችን ከእግዚአብሔር፥ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስም ሰላምና ጸጋ ለእናንተ ይሁን።

፬ፈጣሪዬን ዘወትር አመሰግነዋለሁ፤ በምጸልየው ጸሎትም ሁልጊዜ አስብሃለሁ። ፭በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ፥ በቅዱሳንም ሁሉ ዘንድ ያለህን ሃይማኖትህንና ፍቅርህን ሰምቻለሁና። ፮በኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኘውን መልካሙን ነገር ሁሉ በማወቅ የሃይማኖትህ አንድነት የጸና ይሆን ዘንድ እጸልያለሁ። ፯ወንድሜ ሆይ፥ የቅዱሳን ሰውነት በአንተ ዘንድ ዐርፋለችና በፍቅርህ ብዙ ደስታንና መጽናናትን አግኝቻለሁ። ፰ስለዚህም የጽድቅን ትእዛዝ አዝዝህ ዘንድ በክርስቶስ ታላቅ ባለሙአልነት አለኝ። ፱ይልቁንም እኔ ጳውሎስ ሽማግሌው፥ አሁንም ደግሞ እንደምታውቅ የኢየሱስ ክርስቶስ እስረኛ የሆንሁ ስለ ፍቅር እማልድሃለሁ።

## ስለ አናሲሞስ

፲በእስራቴ ስለ ወለድሁት ልጄ ስለ አናሲሞስ እማልድሃለሁ። ፲፩አስቀድሞ አልጠቀመህም ነበር፤ ዛሬ ግን ለአንተም ለእኔም እጅግ የሚጠቅም ሆኖአል። ፲፪አሁንም ወደ አንተ ልኬዋለሁ፤ ልጄ እንደ መሆኑ[፪] ተቀበለው። ፲፫በወንጌል ስለ ደረሰብኝም እስራቴ ባንተ ፋንታ ያገለግለኝ ዘንድ በእኔ ዘንድ ላኖረው እፈቅድ ነበር። ፲፬ነገር ግን በጎነትህ በፈቃድህ እንጂ በግድ እንዳይሆን አንተ ሳታውቅ ምንም ላደርግ አልወደድሁም።

፲፭ስዘለዓለም ይሆንህ ዘንድ ስለዚህ ምናልባት ለጊዜው ተለይቶህ ይሆናል። ፲፮ከእንግዲህ ወዲህ እንደ ባሪያ አይደለም፤ ነገር ግን ለእኔ የተለየ የተወደደ ወንድሜ ከሆነ ለአንተማ ይልቅ በሥጋውም፥ በጌታችንም ዘንድ ከባሪያ የሚሻል የተወደደ ወንድም እንዴት አይሆንም? ፲፯እንግዲህ አንተ ወንድሜ ከሆንህ እንደ እኔ ተቀበለው። ፲፰የበደለህ በደል ቢኖር ግን ወይም የሚከፍልህ ዕዳ ቢኖር፥ በእኔ ላይ ቍጠረው። ፲፱እኔ ጳውሎስ፥ "ስለ እርሱ እከፍላለሁ" ብዬ በእጄ ጽፌአለሁ። ራስህን እንኳ ልትሰጠኝ ይገባኛል አልልህም። ፳አዎን፥ ወንድሜ ሆይ፥ በጌታችን ስለ አንተ ደስ ይለኛል፤ እኔንም ደግሞ አሳርፈኝ፤ ሰውነቴንም በክርስቶስ ደስ አሰኛት።

፳፩በመታዘዝህ ታምኜ፥ ካዘዝሁህም ይልቅ እንደምትጨምር ዐውቄ፥ ጻፍሁልህ። ፳፪ከዚህም ጋር የማርፍበትን ቤት አዘጋጅልኝ፥ በጸሎታችሁ እግዚአብሔር መንገዴን እንደሚያቀናልኝ፥[፫] ከእናንተም ጋር እንደሚያገናኝኝ አምናለሁ።

፳፫በኢየሱስ ክርስቶስ ከእኔ ጋር የተማረከ ኤጳፍራስ ሰላም ይልሃል። ፳፬በሥራ የምንተባበር ማርቆስ፥ አርስጠርኮስ፥ ዴማስና ሉቃስም ሰላም ይሉሃል፥ ፳፭የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን።

ወደ ፊልሞና የተላከች መልእክት ተፈጸመች፤ በሮሜ ተጽፋ በአናሲሞስ እጅ ተላከች።

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። አሜን።

---

፩ ግእዙ "ለልጁ አክርጳ" ይላል።

፪ ግሪኩ "ልቤ እንደሚሆን" ይላል።

፫ "መንገዴን እንዲያቃናልኝ" የሚለው በግሪኩ የለም።

፪ ቆላ. ፬፥፲፯።   ፲ ቆላ. ፬፥፱።   ፳፫ ቆላ. ፩፥፯፤ ፬፥፲፪።   ፳፬ ሐ. ሥ. ፲፪፥፲፪፤ ፳፭፤ ፲፫፥፲፫፤ ፲፭፥፴፯-፴፱፤ ፲፱፥፳፱፤ ፳፯፥፪፤ ቆላ. ፬፥፲፥፲፬፤ ፪ጢሞ. ፬፥፲፥፲፩።